## የአውሮፕላን ማረፍያው ንድፍ እና የማማከር ስራ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ከዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅቱ ዳር አል ሀንዳሳ ጋር የማማከር ስምምነት የተፈራረመ ሲሆን የአውሮፕላን ማረፊያው ንድፍ በዛሃ ሃዲድ አርክቴክትስ ተሰርቷል።

## የአካባቢ ጥበቃ የዘላቂነት ስትራቴጂ

የአየር ማረፍያው የአካባቢ ጥበቃ እና ዘለቄታማነት ስትራቴጂ የፀሃይ ሃይል መጠቀምን፣ ሃይል ቆጣቢ ስርዓቶችን እና አነስተኛ የበካይ ጋዝ ልቀት ያላቸውን አሠራሮች ቅንጅት በውስጡ የያዘ ሲሆን የፍሳሽ ውኃን ሙሉ በሙሉ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እና የጎርፍ (የዝናብ) ውኃ አጠቃቀም ስርዓትን ያካተተ ነው።




www.ethiopianairlines.com
CorporateCommunication@ethiopianairlines.com
(251-11)517-8913/8165/8907


# የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ መረጃዎች

ቢሾፍቱ

ዓለም አቀፍ አዉሮፕላን ማረፊያ

የአፍሪካ የአየር ትራንፖርት

አዲሱ ገፅታ

Ethiopian
የኢትዮጵያ

STAR ALLIANCE

## አዲስ አውሮፕላን ማረፊያ ያስፈለገበት ምክንያት

አፍሪካን ከመላው ዓለም ጋር በማገናኘት ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ የሚገኘው አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት 25 ሚሊዮን መንገደኞችን የማስተናገድ አቅም ያለው ሲሆን ይህ አቅሙን በቅርቡ እንደሚያልፍ ይጠበቃል፡፡ በዚህም ምክንያት በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የመንገደኛ ቁጥር ማስተናገድ የሚችል አዲስ ዘመናዊ ኤርፖርት መገንባት በማስፈለጉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያን የሚደግፍ ግዙፍ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ መገንባትን መርጧል፡፡

## የፕሮጀክቱ ጠቀሜታ

ቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቁ የአቪዬሽን መሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ከብሔራዊ የኢኮኖሚ ህዳሴ አጀንዳ፣ የኢንዱስትሪ እድገት ትልሞች እና የአቪዬሽን ዘርፍ የረዥም ጊዜ እቅዶች ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ በተጨማሪም አዲሱ የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ኢትዮጵያ በዓለም አቪዬሽን ያላትን ቦታ ከፍ ከማድረጉም በላይ በአፍሪካ ሀገራት ነጻ የንግድ ቀጠና ለመፍጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ ያላትን የመሪነት ሚና የሚያጠናክር ነው፡፡ በተጨማሪም ፕሮጀክቱ የንግድ ቀጠናዎችን በማስፋት፣ ቱሪዝምን በማጠናከር እና የሀገራት የአየር ትራንስፖርት ትስስርን በማሳደግ አህጉሪቱን ከተቀረው አለም ጋር ያስተሳስራታል፡፡

## ለአዲሱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ቢሾፍቱ ለምን ተመረጠ?

የሳይት መረጣ ጥናቱ ባመላከተው መሰረት አዲስ የሚገነባው አውሮፕላን ማረፍያ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ መሆኑ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመንገደኛ ፍሰቱን ከአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፍያ ጋር በተሳለጠ ሁኔታ እንዲያስተናግድ ማስቻሉን አመላክቷል፡፡

ቦታው ከባህር ጠለል በላይ ያለው ሁኔታ አስፈላጊ በመሆኑ ከአዲስ አበባ በ40 ኪሎ ሜትር ርቀት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በቢሾፍቱ ከተማ ዙሪያ የሚገኘው ከባህር ጠለል በላይ 1910 ሜትር ከፍታ ያለው ቦታ ምቹ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## የአውሮፕላን ማረፍያው አቅም

ቢሾፍቱ አውሮፕላን ማረፍያ በመጀመሪያው ምዕራፍ በዓመት 60 ሚልየን መንገደኞችን የማስተናገድ አቅም የሚኖረው ሲሆን በቀጣይ ምዕራፍ 110 ሚልየን መንገደኞችን የሚያስተናግድ አቅም በመፍጠር ኢትዮጵያን ከዓለም አቪዬሽን መሪዎች ተርታ የሚያስቀምጥ ነው፡፡

### የፕሮጀክቱ ወጪ

የቢሾፍቱ አውሮፕላን ማረፍያ የመጀመሪያ ምዕራፍ 12.5 ቢልየን ዶላር በጀት የተያዘለት ሲሆን ወጪው ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት የሚችል ኤርፖርት ለመገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም መሠረተ ልማቶችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን፣ የየብስ ትራንስፖርት፣ የኤርፖርት ከተማ መሠረታዊ ግንባታዎችን እንዲሁም ለሥራ ዝግጁነት አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡

## የፕሮጀክቱ የፋይናንስ መዋቅር

የኢትዮጵያ አየር መንገድ 30 በመቶውን የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት የግንባታ ወጪ የሚሸፍን ሲሆን ቀሪው 70 በመቶ የሚሆነው በልማት የፋይናንስ ተቋማቶች (Development Finance Institutions)፣ በወጪ ንግድ የብድር ኤጀንሲዎች (Export Credit Agencies) እና የንግድ ማኅበራት (Commercial Syndication) ጥምረት የሚሸፈን ነው፡፡

የአፍሪካ ልማት ባንክ (AfDB) የብድር ፋይናንስ መሪ አስተባባሪ ሆኖ የተመረጠ ሲሆን KPMG ደግሞ የፋይናንስ አማካሪ ሆኖ ተመርጧል፡፡

## መልሶ ማስፈር እና ማቋቋም

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ከክልሉ መንግሥት ጋር በመተባበር፤ ዝርዝር ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የመሬት አቀማመጥ ጥናቶችን በማካሄድ፣ በልማቱ ምክንያት ለተነሱ አርሶ አደሮች በሚያረካ መልኩ የሰፈራ እና ኑሮ መልሶ ማቋቋም ስራ ተሰርቷል፡፡